# የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት(መኢአድ) በጎፋ ልዪ ዞን በሳውላ ከተማ የጠራው የተቃውሞ ሰልፍ እጅግ በተሳካና በሰላም ተጠናቀቀ።

የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ) በደቡብ ኢትዮጵያ በመኢአድ አመራርና አባላት ላይ የወያኔ ካድሬዎችና ባለስልጣኖች የሚያደርሱትን በግፍና ያለአግባብ ማሰር፣ ማፈናቀል፣ መደብደብና ማንገላታት በመቃወም ግንቦት ሶስት ቀን 2006 ዓ/ም በሳውላ ከተማ የተቃውሞ ሰላማዊ ሰልፍ ጥሪ በማድረጉ፤ በጎፋ ልዩ ዞን 12 ወረዳዎች የሚገኙ የመኢአድ አባላትና ደጋፊዎች ተጉዘው በመምጣት ከተማዋን ያናወጠ፣ እጅግ የተሳካና ሕዝብ ምሬቱንና ቁጣውን የገለጸበት የተቃውሞ ሰልፍ አካሂዷል። ሰላማዊ ሰልፉ እንዳይሳካ በፖሊስና በካድሬዎች የተደረገውን መሰናክልና ችግር ጥሶ በማለፍ ሰልፉን እንደተካፈለም ታውቋል።

ከአዲስ አበባ ተጉዘው ሕዝቡን ሲቀሰቅሱ የነበሩት የመኢአድ አመራር የፓርቲውን ፕሬዚዳንት ጨምሮ በትላንትናው እለት በፖሊስ ግማሽ ቀን ታግተው እንደነበረና ሕዝብ በፖሊስ መታገታቸውን ሰምቶ ፖሊስ ጣቢያውን በመክበቡ የተደናገጡት ፖሊሶች፣ በሉ ‘ወያኔ” እንዳትሉ በቅስቀሳችሁ ላይ እንዲሁም ነገ ጠዋት ሁለት ሰዓት ጀምራችሁ አምስት ሰዓት ላይ እንድታቆሙ ለነገሩ ሕዝቡ ገና ከአሁኑ ከተማዋን አጥለቅልቋታል ነገ ትላላችሁ እንጂ  ሰልፉን እኮ ጀምራችሁታል’ በማለት ለቀዋቸዋል።

በትላንትናው እለት ከተማዋንና አካባቢውን ሲቀሰቅሱ ውለውና አምሽተው ወደ ማረፊያቸው ቢሄዱም ከገጠር ስንቁን ቋጥሮ ከ280 ኪሜ በላይ ተጉዘው የመጡ ከ500 በላይ ሰልፈኞች ሰው የሚያውቁ በየሰው ቤትና በረንዳ የሌለውም በየጥጋጥጉ በቡድን በቡድን በመሆን ሜዳ ላይ አድሮ ጠዋት ከአንድ ሰዓት ጀምሮ ተሰባስቦ ከጥዋቱ ሁለት ሰዓት ሲሆን ሰልፉ ተጀምሮ ከቅርብም ከሩቅም እየመጣ ወደ ሰላሳ ሺህ የሚገመት ሕዝብ ሰልፉን መቀላቀል ጀመረ። የተለያዩ መፈክሮችን ባካባቢው ቋንቋና በአማርኛ በማሰማት ንዴቱንና ቁጣውን በመግለጽ እስከ ጠዋቱ አምስት ሰዓት ተኩል ከተጓዙ በሁዋላ ወደ መሰብሰቢያ ስፍራ በማምራት ላይ እንዳሉ ከየወረዳው መጥተው ሰልፉን እንዳይቀላቀሉ በየኬላው ላይ በፖሊሶች ተይዘው የነበሩት ሰልፉ አልቋል ብሎ ፖሊስ ሲለቃቸው በአንድ አቅጣጫ ብቻ ከወይዳ ወረዳ የመጡ 2000 ሰዎች በጭፈራና በዜማ ሰልፈኛው በመንገድ ላይ እንዳለ እንደ አዲስ ደራሽ ጎርፍ በመድረስ ሰልፈኛውን ተቀላቅለዋል።

ሰልፈኞቹ ከሚሏቸው መፈክሮች በጥቂቱ፤

ሕዝባዊ አንድነት ለነፃነት!
አምባገነን በሕዝብ ይሸነፋል!
ወያኔ/ኢህአዴግ በሰላማዊ ትግል ይሸነፋል!
ሕዝብ አሸናፊ ነው!
የፖለቲካ ልዩነት ወንጀል አይደለም!
ፍትህ አጣን!
አንድ ኢትዮጵያ! አንድ ሕዝብ!
የመሳሰሉትንሲያሰሙና ባካባቢው ቋንቋ ደግሞ ሲዘምሩና መፈክር ሲሉ ተደምጠዋል። የሕዝቡን ቆራጥነትና የጋለ ስሜት መገመት ከሚቻከው በላይ እንደነበር አመራሩ ገልጿል።

ከዚያም ወደ መሰብሰቢያ ስፍራቸው ከደረሱ በሁዋላ ከተለያዩ ወረዳዎች የመጡ አባሎች ንግር ካደረጉ በሁዋላ የመኢአድ ምክትል ፕሬዚዳንት አቶ እንድሪያስ ኤሮ እንዲሁም ፕሬዚዳንቱ አቶ አበባው  መሐሪ ለተሰብሳቢው ሕዝብ ንገግር አድርገዋል።

ሰልፈኛው በሰላም ካሰናበቱ በሁዋላ የመኢአድ አባላት ቀርተው በወሳኝ ጉዳዩ ላይ የመኢአድ ጽ/ቤት ፊት ለፊት ባለው ሜዳ ላይ ውይይተው አካሄደው ሲያበቁ በሰላም ሁሉም ወደየቤቱ ተመልሷል። የመኢአድ ደጋፊዎች በካናዳ የሰልፉን አካሄድ በስልክ በመከታተል በደብተራው የፓልቶክ ክፍል በቀጥታ ሲያስተላልፉ ቆይተዋል።  የሰልፈኛው ፎቶና ቪዲዮ ይከተላል።